# <u>ጉድ በል ሀገሬ!</u>
# (ከጃማ ጦስኝ)

የቤተ ዘመዱ፣ የጓደኞች ደስታ፣
ሰፈሩን አደምቆት፣ በሆታ በዕልልታ፣
ዘመድ አዝማድ ኮርቶ፣ ነገ በሚሆነው፣
የሙሽራው እድል፣ ሲወራ በሰፊው ፣
“እሱ እድለኛ ነው ፣ አገኘ የተማረች፣
የፈረንጁንም አፍ፣ ጠንቅቃ ያወቀች፣
ከነጮቹ ሀገር፣ ባህር ማዶ ሄዳ፣
ሰልጥና የመጣች፣ ድንቅዬ ኮረዳ፣”
እያለ ሰው ሁሉ፣ ይኸንን ሲያወራ፣
ሙሽሬም ቸኩሎ፣ ሊሆን አባወራ፣
ሰርገኛ እደምተኛው፣ እንዲህ ሲተራመስ፣
ጫጉላ ቤቷንም ፣ ገጠሟት ትርምስ::
ሚዜዎቹን ሁሉ፣ “ወጡልኝ እያለ”፣
ሙሽሪትን አቅፎ፣ ማባበል ጀመረ::
የተራቡ ዓይኖቹም፣ ሊያያት እጅግ ናፍቆ፣
የልቡን ትርታ፣ ይዞታል አምቆ::
“ሚዜ ሙሽራዬ፣ ልቤ ያፈቀረሽ፣
አሣይኝ ዓይንሽን፣ ከእንግዲህ የኔ ነሽ::”
እያለ በጉጉት !!!!!!!
ከንፈሯን ለመቅመስ እንዲያ እንደተራበ፣
ዓይነርግቧን ገልጦ ሶስት ጊዜ አማተበ ::
ዓይኗ ስለት አለው፣ እንዳገዳ ልጫ፣
ሊደፍራት አልቻለም፣ የነካውን እንጃ፣
ወይ ወበቷ ይሆን?! ወይ ጠንካራነቷ?!
እንዲህ ድርቅ አደርጎ፣ ያስቀረው ክፉቷ?!
የቆመበት ቦታ፣ መሬት ቢጠበውም ፣
ይጋፈጠል እንጂ፣ ማምለጫየለውም ፣
እሩቅ በሩቅ ሆነው ፣ ሳይደፋፈሩ፣
ያቺን የደስታ ቀን፣ እንዲህ አከበሩ ::
ጫጉላውን ከበው ፣ ሚዜዎች በሙሉ ፣
ሆታውን ሊያቀልጡት፣ ካሁን አሁን ሲሉ ፣
ብር አምባር ሰበረ፣ ብለው ሊፎክሩ ፣
ጋኑን ሊያስከፍቱ ፣ ሙክቱን ሊጥሉ ፣
ዙሪያውን በዞሩ ፣ ወዲያ ወዲህ ቢሉም ፣
ከሙሽሮች በኩል ፣ ነገር ግን መልስ የለም ::
“አይ ወንድሜ !! አይደረግም !
ይኸስ !በቤታችንም የለም ! ”
**እየተባባሉ ሲተረማመሱ ፣**
ባህላቸውን እያወደሱ፣
ሰዓት አሳልፎ፣ እጂጉን ቆይቶ፣
ብቅ አለ ሙሽራው ፣ ሜፈጡን ጠልቶ ::
“ምንድነው ችግሩ? ደንግጠህልሳ፣

ግራ ተጋብዙናል፣ ባንተ የተነሳ::
ምነው ? ምን አገኘህ ?
ደህና ነው የቆየህ?!”
ብሎ ቢጠይቀው ፣ ተቻኩሎ ለወሬ፣
“እባክህ ዝም በል!
የገጠመኝን ጉድ እንዳትሰማ አገሬ!”
አለና በንዴት፣ እያንቀጠቀጠው ፣
የልቡን ደም ፍላት፣ መልሰና ዋጠው ::
“እህ ህ ምንድነው እሱ?
ንገረን ደስታወን!
ጭሩላ ቤት የሆነውን !
አገኘህት በክብሯ ?
አስረክብ የደማን ሸማ ፣
ባህላችን እንዳይታማ ፣
እኛም እናሞገሳት፣
ለእናት ለአባቷም ክብር ናት :: ”
ብሎ ነፍሱን ቢያስጨቀው ;
መኻራው ለመናገር፣ አፉን ደምደም አለው ::
ወይ ትልቅ በሽታ ከነጬ የተጋባው ፣
ለካስ እንዴ ሴ ...ት .. የሆነው ወ ...ን ...ዱ .. ነው !!!!!!!!!!!!!!!!!!!!!
እግዚኦ በሉ!” አለው::